# የመፀዳጃ ቤት አሰራር

## የጉድጓድ አቆፋፈር፣ መክደን፣ ከለላ አሰራርና የመታጠቢያ ዝግጅት

### 1. የጉድጓድ አቆፋፈር





ጉድጓድ የሚቆፈረው ከመኖሪያ ቤት ጓሮ 6 ሜትር ራቅ ብሎ ሊሆን አቆፋፈሩም የዋንጫ ቅርፅ እንዲኖረውና ስፋቱ 90 ሳንቲ ሜትር ጥልቀቱም እንደአፈሩ ሁኔታ ቢወሰንም ከ3 ሜትር መብለጥ የለበትም።

### 2. ጉድጓዱ እንዳይናድ ማጠናከር



ጉድጓዱ ተቆፍሮ ካለቀ ቡኋላ ዙሪያውን ሰፋ አድርጎ በመቆፈር በድንጋይ ካብና ጭቃ እየገነቡ ከመሬት በላይ ብቅ ብሎ እስከሚታይ መገንባት በላዩ ላይ እንጨት መረብረብ።



በጉድጓዱ ልክ ሳጠራ ሰርቶ የጉድጓዱን አፍ መገንባት።

### 3. ለጉድጓዱ መከደኛና ከላላ መስራት



ጉድጓድ እንዳይናድ የሚደረገውን ካድረጉ ቡኋላ ጠንካራና ቁመታቸው ከጉድጓዱ አፍ ቢያንስ 50 ሳንቲ ሜትር ወጣ ባሉ እንጨቶች በቅድሚያ በማዘጋጀት ለሰገራ መውጫ 20 ሳንቲ ሜትር በ15 ሳንቲ ሜትር የሆነ ቀዳዳ በመተው መክደን።



ዙሪያውን ግድግዳ ሰርቶ ለጣሪው ክዳን አበጅቶ ወለሉንና ግድግዳውን በጭቃ ወይም በእበት መምረግ።

### 4. የሽንት ቤት ቀዳዳ ክዳንና የእጅ መታጠቢያ መስራት



ለሰገራ መውጫ ክዳን በመስራትና የእጅ መታጠቢያ በማዘጋጀት መጠቀም።



መፀዳጃ ቤቱን በየግዜው ማፅዳት ከለላውን መጠገንና ከሽንት ቤት መልስ እጅን በአመድ ወይም በሳሙናና በውሃ መታጠብ አይርሱ። መፀዳጃ ቤቱ እንዳይሸት በየቀኑ ትንሽ ትንሽ አመድ መጨመር አይርሱ።

# ለጤናችን ለክብሩቻችን በመፀዳጃ ቤት መጠቀም ይሁን ባህላችን!!

1. መፀዳጃ ቤቱን በየእለቱ ማፅዳት፡፡
2. መጥፎ ሽታ ለመከላከል ከቤት ውስጥ የሚፈጠር አመድ ሁልግዜ መፀዳጃ ቤቱ ውስጥ መጨመር፡፡
3. መፀዳጃ ቤቱን መላው ቤተሰብ እንዲጠቀምበት ማድረግ፡፡
4. ህፃን ልጅዎን አይንምድር በፖፖ ከማስወጣትዎ በፊት ፖፖው ውስጥ አመድ ወይም ቅጠል ይጨምሩ የተወጣንም ሰገራ ወዲያውኑ መፀዳጃ ቤት ውስጥ ይጨምሩት፡፡
5. ለመፀዳጃ የተጠቀሙበትን ወረቀት ወይም ቅጠላቅጠል መፀዳጃ ቤቱ ውስጥ ሁልግዜ መጨመር፡፡
6. ተፈላጊውን ከለላና ምቾት እንዲሰጥ የመጸዳጃ ቤቱን ግድግዳና ጣራ ሁልጊዜ መጠገን ያስፈልጋል፡፡
7. በመፀዳጃ ቤቱ ከተጠቀሙ ቡኋላ እጅዎን በሳሙና ወይም በአመድ መታጠብ ሊረሳ የማይገባው ተግባር ነው፡፡

(ውሃ ቆጣቢ የእጅ መታጠቢያ አስራርን በተመለከተ ተያይዞ የሚገኘውን መመሪያ ይመልከቱ፡፡)

USAID FROM THE AMERICAN PEOPLE | HIP HYGIENE IMPROVEMENT PROJECT

wsp water and sanitation program